# ሦስተኛው ሥጋቴ ይህ ነው "ብድር በምድር" ሲከፈል

**ደምለው አልማው**

October 28, 2016

በመጀመሪያ መጻጽፌ ሥጋቴ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስልት አውጥቶ ወደ አንድነት መጥቶ ኃይል አመንጭቶ ካልታገለ የትም እንደማይደርስ እና የኢትዮጵያን ሕዝብ መስዋእትነትን ከንቱ እንደሚያስቀር ስለተሰማኝ ሥጋቴን ለመግለጽ ሞከርኩ::

ሁለተኛ ሥጋቴን የገለጥኩት የኦሮሞን ሕዝብ እንቅስቃሴን የተመለከተ ነበረ:: እንደሚታወቀው የኦሮሞ ትግል ቅርቃር ውስጥ ገብቶ ለብዙ ዓመታት እንደኖረ ይታወቃል:: የኦሮሞ ትግል የተደበላለቀ መንፈስ አለው:: ኦሮሞ የምትባል አገር ለመመስረት የሚታገሉ: መሠረታዊ የሆኑ የዴሞክራሲ: የፍትህ እና የፌዴራሊዝም ሥርዓትን ለማረጋገጥ የሚታገሉ: ኦሮሞን ወደ ጥንታዊና ባህላዊ አገዛዝ ለማስመለስ የሚታገሉ እና ሁሉንም በመቀበል ድብልቅ አቋዋም ይዘው ወደፊት የሚራመዱ ኃይሎች መካከል የአቋዋም ጥራት አይታይም::

በዚህ ላይ አንዳንድ ግለሰቦች ተዋቂነትንና ንዋይን ለማግኘት የኦሮሞ ልብን ለማሞቅ እያሉ የቆየ የሕዝቦችን በደል እየጠቀሱ ለወቅታዊ የቅስቀሳ ፍጆታ እየተጠቀሙ ኦሮሞን ጠባብ የሚያሰኙ: ኦሮሞን በሌላው ሕዝብ ዘንድ በጥርጣሬና በሥጋት እንዲታይ እያደረጉ: ዜጎች ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲክዱ በማደረግ የሚያካሂዱት ትግል ዞሮ ዞሮ ጉዳት እንዳለው: ኦሮሞ እየተጨፈጨፈ እያደረገ ያለው ትግል የሚፈለገውን ድልና ውጤት ካላመጣ የኦሮሞ ታጋዮች ሕዝባዊ ቁጣ እንደሚያርፍባቸው ስለታወቀኝ ሥጋት አደረብኝ ብዬ ለመጻፍ ዳዳሁ:: እንደዚሁም የኦሮሞ ሕዝብ በራሱ በቤት ሥራ ከተወጠረ ከሣጥን ውጭ ወጥቶ ለማሰብ ጊዜ ካጣና ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋራ መተባበር ካልቻለ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታን እንደሚወስን ተሰማኝ:: እናም ሥጋቴን ገለጽኩ::

አሁንም ሦስተኛ ሥጋት አድሮብኛል:: ወደ ሦስተኛው ሥጋቴ ከመግባቴ በፊት ያለፉትን ሥጋቶችን ላነበባችሁ ኢትዮጵያውያን ምሥጋናዬ የላቀ ነው::

ሦስተኛው ሥጋቴ እንደሚከተለው ነው:: ሰው ነገ የሚባል ቀን አለው:: ሰው ወደ ነግ ይሂድ ወይም ነገ ወደ ሰው ይምጣ ባይታወቀም ሰው እና ነገ መገናኘታቸው ቁርጥ ነው::ለዚህም ነው የሰው ልጅ እራሱን ከብዙ ነገር ቆጥቦ ለነገ ብሎ የሚያኖረው:: ምክንያቱም ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ የሚያውቀው ከፈጣሪ በስተቀረ የለምና:: ምክንያቱም ዛሬ ያለው ነገ አይኖርም:: ዛሬ የሌለ ነገ ይኖራል:: ሰው ሃሳቢ: አስተዋይ ስለሆነ በዛሬ ላይ ሆኖ ነገንም ይኖራል:: ክፋት: ተንኮል: ሤራና ወንጀል የሚባሉት አሉታዊ ነገሮች ነገን ያበላሻሉ:: በተቃራኒው ያሉት ግን ነገን መልካም ያደርጋሉ:: አነሳሴ ስለ ፍጥረተ-ነገ ማውራት አይደለም::

የሰው ልጅ ሆኖ እንዴት ዛሬ ላይ ቆሞ ነገውን ያበላሻል ለማለት ፈልጌ ነው:: ማነው ያበላሸ ብላችሁ ከጠየቃችሁኝ መልሴ ቀላል ነው:: ዛሬ ቀኔ ነው ብሎ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ የሚገድል: የሚያጠፋ: የሚዘርፍ: የሚገፍ: የሚነውር: የሚያጥላላ የሚያዳላ:

የሚዋሽ: የሚቀጥፍ: የሚቆርጥ: የሚፈልጥ: በሰማይ ፈጣሪን: በምድር ሕግን የማይፈራ ጨካኝ አረመኔ ሆኖ ዛሬን የዋለ ሰው: ነገ ባለተራ ነው:: ትላንት በቁዋንቁዋው ላይ የተቀለደበት: ትላንት በሙያው ምክንያት የተናቀ: ትላንት በአርሶ አደርነቱ ዝቅ ተደረጎ የተገመተ: ትላንት ሰው በዘሩ: በጎሣው: ይበላለጥ እንደነበረ አይዘነጋም::

ምናልባት የትላንት ጌቶች በደሉን ላለመቀበል እና ላለማመን የሚያበሽቅ ክርክር ይገጥሙ ይሆናል:: የአያቶቻቸውን ገመና ለመጠበቅ እና መልካም ሥራዎቻቸውን ብቻ እንዲወሳላቸው የሚፈልጉ የፊውዳል ልጆችና የልጅ ልጅዎች አሉ:: ባለፈው ታሪክ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳንደርስ የእነሱ ድርቅና ዛሬም እንቅፋት ሆኖ የትላንት ጭቁኖች እልህ ውስጥ እንዲገቡ የሚገፋፉ ከታሪክ መማር የማይፈልጉ ክፍሎች ዛሬ በየደረሱበት ጨጉዋራቸው የሚላጥበት: የቀደምቶቹ ታሪካዊ ስህተት በተመዘዘ ቁጥር ራስ ምታታቸው የሚጠናባቸው: ዕዳ ከፋይ ትውልዶችን አይቶ ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው የሚያቆዩት እጅግ አስከፊ በሽታ ዛሬ ሊታወቃቸው ያልቻለ ክፍሎች አሉ:: ዘላለም እንደነገሰ: ዘወትር እንዳየለ አይኖርም:: ብድር በምድር የሚባል አባባል አለ:: አሁንም ዳር ዳርታውን ትቼ ወደ ቁም ነገሬ ልዝለቅ::

ዛሬ በኢትዮጵያ ወያኔ የሚሠራውን ሥራ ሁሉም ሰው ያያል:: ይሰማል:: ያስተውላል:: ይመለከታል:: በዓለም ላይ መጥፎ የተባሉትን ሁሉ ሲሠራ አንዳች ነገር ህሊናው አይቆነጥጠውም :: አውሬአዊ ባህርይ ተላብሶ: በአንድ አምላክ እጅ የተሠራውን: የተከበረውን: ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ መግደልን: አካል ማጉደልን: ደም ማፍሰስን: አስሮ ማሰቃየትን: ማሳደድን: ጀብድ አድርጎ የሚቆጥረው: ዕውቀት መስሎት የሚመጻደቅበት ሰውዋዊ ፍጡር በኢትዮጵያ ምድር አለ ከተባለ ወያኔ እና ወያኔ ብቻ ነው:: ወያኔ ሕገ- ሙሴን ሙሉ በሙሉ ጥሶአል:: አትግደል! የሚለውን ተላልፎ ሺህ ሰው እየገደለ ነው:: አታመንዝር የሚለውን በመጣስ ዝሙትን መዝናኛው አድርገውታል:: ከመጠን አትለፍ የሚለውን ረግጠው ናላቸውን እስኪስቱ ይጠጣሉ::

የባልንጀራህን ወይም የጎረቤትህን ሚስት አትመኝ የሚለውን ከቁብ ሳይቆጥሩ አያሌ የተከበሩ የቤት እመቤቶችን በብልግና ደፍረዋል:: የተቀደሰውን ትዳር አራክሰውታል:: እንዲያውምየምድር ህግጋትን በሙሉ ደምስሰዋል:: ልባቸው ስለተደፈነ እምሮአቸው ሚዛኑን ስለሳተ ከእውነት እጅግ ስለራቁ ከሰውነት ወደ እንስሳዊ ባህርይ ወርደው ሥጋቸው ያዘዛቸውን ሁሉ ይፈጽማሉ :: አንዳንዴ ከአእዋፋት ውጭ ባለሁለት እግር ልዩ እንስሳ በዚህ ፕላኔት ይኖር ይሆን የሚያስብሉ ናቸው:: አንዳንዴ ትግሬነት እንዲህ ነበረ እንዴ የሚያሰኙ ናቸው::

እንግዲህ ወያኔ እንዲህ ዓይነት እርኩስ መንፈስ የተጠናወታቸው ሰዎች ስብስብ ሲሆን: ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ አንድን ሕዝብ ተገን አድርገው እየተጠቀሙበት ነው:: ለመጣባቸው አደጋ ሁሉ የትግራይን ሕዝብ ቤዛ ማድረግ ይፈልጋሉ:: የትግራይን ሕዝብ መገን እያደረጉ ሲገለገሉበት እራሳቸውን ሚሊዮነር ሲያደርጉ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ግን ማለትም እዚያው ቆላ ያለው የተምቤን: የአጋሜ: የአዲግራት ገበሬ ያው ገበሬ እንደሆነ አለ:: ይሁን እንጂ በትግራይ በተተከለ ፋብሪካ ጉራጌ ሂዶ አይቀጠርበትም:: በአደዋ በሚሊዮን ገንዘብ በተመፈጠሩ ፋብሪካዎች ውስጥ አንድ የኦሮሞ ልጅ ሂዶ ደመወዝተኛ አልሆነበትም:: አንድ የቡሬ ዳሞት ወጣት ሥራ ፍለጋ ብሎ ትግራይ አልገባም::

በአንጻሩ ከወያኔ የተስማማ የትግራይ ሰው ጋምቤላ ሂዶ የመሬት ከበርቴ ሆኖአል:: ቤኒሻንጉል ወርዶ ወርቅ አምራች ተብሎአል:: ኢሉ ባቦራ ገብቶ ቡና አምራች ገበሬ ሆኖአል:: አዲስ አበባ መጥቶ ባለአምስት ኮከብ ሆቴል ባለቤት ለመሆን

ታድሎአል:: በሚሊዮን የሚቆጠር ኩባንያ መስርተዋል:: ሳይማሩ ባለኮሌጅ ሆነዋል:: በወያኔ ዘመን ትግሬ መሆን የወርቅ ቁልፍ መሆን ነው :: ለትግሬ የማይከፈት በር እና ካዝና የለም:: ባንኩ: እንሹራንሱ: ጉሙሩኩ : ኢሚግሬሽኑ: ማዘጋጃ ቤቱ: ጨው ምርቱ: እንዲያውም ቤተ-ክርስቲኑ ሁሉ በትግሬ ሰው ተሞልቶአል: ልደታ በ/ክርስቲያን ሂዱና እዩ :: ቦሌ መድኃኒ ዓለም ቤተክርስቲያን ተመልከቱ:: በሁሉም አድባራት ያለ ዕውቀት በትግሬነት ብቻ ተይዞአል:: ስም ለማጥፋት አይደለም:: ወያኔ አዲስ አበባ ከገባ ወዲህ በትግሬ ሰዎች የተሠሩ የአዲስ አበባ የዘመናዊ ፎቆች: ታወሮች: ባለቤት እነማን እንደሆነ በስም ዝርዝር ፎቅን የሚያክል ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል::የቀበሌ ቤትና የኪራይ ቤቶች ታሪክ በኢትዮጵያ ብቻውን የአድልኦ ማረጋገጫ ነው:: እንኩዋን መከላከያ :እንኩዋን አየር መንገድ: እንኩዋን ቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤቶች ውስጥ የገቡ ትውልደ ደብዓዊያንን መመልከት ይቅርና::

ዛሬ እስከ ግማሽ ሚሊዮን ብር እየተከፈለላቸው በህገ ወጥ አሜሪካ; ካናዳ: አውስትራሊያ: እንግሊዝ: የትም ወደ አደጉ አገሮች የሚጉዋዙት ደብዓዊያን ናቸው:: ዛሬ የአራተኛ ክፍል የሸሬ ወጣት ሞተርስ ካምፓኒ ባለቤት ነው:: ዱባይ ቅንጦት ሆቴል ውስጥ ተቀምጦ ንግዱን ያካሂዳል:: እኔ በግሌ የማውቀው የአንድ ቤተክርስቲያን መሬትን እኩል ከፍሎ በመውሰድ ወደር የሌለው ፓላስ የሠራበት ሰው አውቃለሁ:: እስቲ አዲስ አበባ ጦር ኃይሎችን አልፍ ብሎ ወደ ፌስቱላ ሆስፒታል በሚወስደውና ወደ ወየራ በሚያሻግረው መንገድ ላይ አውግስታን አለፍ ብላ ባለችው ቤተክርስቲያን ጉዋሮ ያለውን ተዓምር ተመልከቱ :: እሱ ብቻውን የኢትዮጵያዊያንንና በሥርወ- ወያኔ ተጠቃሚ ማነው ብሎ ለማነጻጸርያ ያህል ድንቅ ምሳሌ ይሆናል:: ኸረ ስንት እና ስንት ጉድ አለ?

ነባር ኢትዮጵያዊ ነጋዴዎችን እንደነ ገብረዩስ ቤኛን / አማልጋሜትድ ሊሚቲድ ካምፓኒ/ እንደነበቀለ ሞላ ሆቴሎችን እና ሌሎችን ነቅለው ካአገር በማስወጣት ሌሎችን አሳብደው እራሱን እንዲያጠፉ: የተቀረውን በአራጣ አበዳሪነት ከርቸሌ በመክተት ቢዝነሱን ቀምተው እንደሚሠሩበት አገር ነው የሚያውቀው:: የትግራይ ሕዝብ ተጠላ ይባላል:: እንዴት?አይጠላ የሌላው ጉሮሮ እየተዘጋ የእሱ እየሰፋ የሌላው ድርጅት እየተዘጋ እሱ አዳዲስ ድርጅት እየከፈተ ሌላው የቢሮ ክራሲ ሰለባ ሲሆን እሱ እቤቱ ቁጭ ብሎ በተላላኪ እና በስልክ ጉዳዩን ከጨረሰ ሌላው ባላተረፈው ገቢ ከባድ ግብር ተጭኖበት ሲከስር እሱ በነጻ ፈቃዱን ሲያሳድስ ሌላው ጻፍክ ተብሎ በአሸባርነት ሃያ ዓመት ሲፈረድበት እሱ ልማታዊ ሚዲያ እየተባለ የአገርና የሕዝብ ገንዘብ ተዝቆ ሲሰጠው : እያለ…… ብዙ ብዙ አብነቶችን መዘርዘር ይቻላል:: እንዲያውም ያደክማል:: በአንድ አገር እየተኖረ ሌላው እንደካሮት ቁልቁል ወደምድር ሲሰርግ: የትግሬ ሰው እንደ ሮኬት ወደሰማይ ሲመነጥቅ እንዴት አይነገር ይባላል? ግፉ እራሱ አፍ አውጥቶ ይናገራል እኮ?

የትግሬ ሰው ይህን ሁሉ እድል ሲያፍስ ሌላው ወገኑ በችጋር ሲጠበስ እግዚአብሄርን እንኩዋን ያልፈሩ ኢ-ፍትሃዊ ባለህብቶችና ቱጃሮች ሲሆኑ: ነገ የሚባል ቀን ሲመጣ ምን እንሆናለን አላሉም:: አሁን አሁንማ ጳጉራቸውን ለማስከርከምና ውሽሞቻቸውን ለመወሸም ዱባይ ደርሰው መመለስን አቃቂ ደርሶ መልስ ያስመሰሉ አሉ:: ሽምበቆ የመሳሰሉ የዩክሬን ለጋ ወጣት ሴትኛ አዳሪዎችን ቅምጥ አስቀምጠው የሚዝናኑ የትግራይ ወያኔያዊ ኢንቨስተሮች ሲፈጠሩ ምን ተብለው ይጠሩ??

የትግራይ ሰው በወያኔ ዘመን የሥርዓቱ ባለቤት ሆኖ በቆየበት አልተጠቀመም ብሎ መናገር ህሊና አይፈቅድም:: ሌላው ቀርቶ ውጭ ያለው ዳያስፖራ ትግራይ በአገር ቤት የሚያንቀሳቅሰው ሀብት ቀላል አየደለም:: ያ ሀብት እኮ ነው ማመዛዘን የሚባለውን ከጭንቅላታቸው ውስጥ ፍቆ ያጠፋው:: እነሱ ስለደላቸው የባሌ ሰው ደልቶታል:: የሀራርጌ ሰው ተመችቶታል:: የወሊጋ ሰው በፍስሃ

ላይ ይንከባለላል:: የጎጃም ሰው በተድላ ተጨማልቆአል ብለው ያስባሉ:: ማሰብ ብቻም ሳይሆን ደፍረው ይናገራሉ:: እውነት የሚባል ነገር የለም:: እንዲያውም እውነት የሚባል ቃል ኮንትሮቨርሺያል የሆነ ሃሳብ አድርገው ሳይወስዱት ይቀራሉ? እነ ምንተስኖአቸው ::

ለዚህም ነው በሃያ አምስት ዓመታት የሙብት ጥሰት: የግድያ: የአፈና: የእስራት: የድብደባ: የገፈፋ: የዘረፋ: የነጠቃ ተግባርን በፍጹም መቃወም ያልቻሉት:: እንዲህ ሲል በትግራይ ደሀ የለም ማለቴ አይደለም:: እንደዚያ ከተባለማ ኒውዮርክ ጎዳና ላይም በረንዳ አዳሪ ሞልቶአል:: በርክሊይ ካሊፎርኒያም እኮ የሆም-ለስ ከተማ ነች::

ዛሬ መላው አምሐራና መላው ኦሮሞ ከመላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ጋራ አንድ ሆኖ መንቀሳቀስ ሲጀምር: በኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት ከጎንደር መቀሌ ድረስ በቦይንግ ተጉዋጉዘው ሲያበቁ ስደተኛ ተብለው የሶማሌ ክልልን በጀት በመቀልበስ ወሰዱ:: የሞተው የጎንደር ሰው ካሳ አይፈልግም:: የተፈናቀለው ትግሬ በእግር ገብቶ በቦይንግ የወጣው ተጎጂ ሆነና ተካሰ:: ከዚህ በላይ ዘረኛ እና አድልኦ ፈጻሚ ሥርዓት አለ? በደም ይትግራይ ሕዝብ ግማሽ የሚያክለውን የኦሮሞ ሕዝብ ገደል ጨምረው ሲያበቁ ዓለም ኢትዮጵያ ማቅ ለብሳ ሲታነባ እነሱ ወደመቀሌ ተጉዋዙ:: በመጀመሪያ ማን ውጡ አላቸው? ጅብ ሌሊት የሠራውን አውቆ ቀን ይደበቃል ካልተባለ በስተቀር::

እንዲህ እንዲህ እያሉ አገሪትዋን ዘርፈው እየጨረስዋት ነው:: ለነገሩ የቴሌኮሙኒክሽን ዋና ቋዋቱ ወደ ትግራይ ከሄደ ቆየ:: የአግሪትዋ ብሄራዊ ባንክ ግምጃ ቤት ወደ መቀሌ ከተዛወረ ሰነበተ:: የአገሪትዋ መከላከያ ኃይል እንደዚሁ ከሌላው አከባቢ ተነቅሎ ሲወሰድ ለምን አለተባለም:: አሁን የቀራቸው አዲስ አበባ የሚገኙ ኤምቢሲዎችን ማዛወር ነው:: ሽገርን የጦርነት ቀጠና በማድረግ መቀሌን ካፒታል ለማድረግ ወያኔ አላሰበም ካላችሁ የዋህነት ነው::

ትግራይ ሪፐብሊክ ምሥረታ እየተጋመሰ ነው:: አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ እስካሁን መጠባበቂያ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ታግሎ የተዘረፈውን እንዳይመልስ አዲስ አበባን ለቢጤዎቻቸውና የመገንጠል አባዜ ለተጠናወታቸው የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ማፈሪያዎች አስረክበው ቢሄዱ ቅድሚያ የመቀመጫዬን እንዳለችሁ ዝንጀሮዋ ሆነን ወደ እርስ በእርስ ፍጅት አንገባም ትላላችሁ? ወያኔ ከሌለ ሶማሊያ ትሆናላችሁ የሚሉ አሜሪካኖች ከምን መነሻ ሃሳብ ነው ብለን ለምን አንጠረጥርም?

ይህ እንዳይሆን የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ወንድምነቱን አልፈለገም:: በክፉ ቀን አብሮ መቆምን አልወደደም:: የኢትዮጵያ እናት ስታለቅስ እነሱ ነፍሰ-ገዳይ ጋራ እስክስ ሲሉ ነው የሚታዩት:: አስረሽ ምቺው ማለት ይሄ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያልቅ የትግራይ ሕዝብ ከበሮ ሲደልቅ: የኢትዮጵያ እናት ሲታለቅስ: የትግራይ እናት ስትል እስክስ: ይሄ ያቀባብራል? ይሄ ያስተሳስባል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላለም ለትግራይ ረኃብ ከጉሮሮው እየቀነሰ ሲለግስ: ሲረዳ የኖረው ሕዝቤ ወገኔ ብሎ ነበረ:: ሞቴን የሚመኝ ሕዝብ ልርዳ ብሎ አልነበረም:: በመሀል አገርም ትግሬዎች ተጋብተው ወልደው ከብረው በሀብትም በልጽገው ሲኖሩ የበደላቸው ሕዝብ አለ? አቶ ዳንኤል መብራቱ ነቃሽ ሁን እስቲ:: ብቸኛ የሊፍት ካምፓኒ የዳን ቴክኖክራፍት ባለቤት ሆነህ ስትሠራ ሥራውን ነጥቆህ ለዘሩ የሰጠ ሥርዓት ነበረ? እንዲያውም የኦሮሞ ቆንጆ አግብተው ተንደላቅቀው ሲኖሩ ነው

የምናወቀው:: ዛሬ ትግሬ የሆነ ሰው በአሜሪካ ሪል ስቴት ውስጥ ገብተዋል:: በአውሮፓ ቢዝነስ ውስጥ ሰርገዋል:: በአፍሪካ አገሮች ውስጥ ወዳጅ አፍርተዋል:: ገንዘብ ካለ በሰማይም አስፋልት አለ የሚባለውን ተረት እነሱ ተጠቅመውበታል::

እኔን ያሳሰበኝ እና ሥጋቴ የሆነው እውን ይኸን ሁሉ አድርገው በአንድ አገርም ባንኖርም እንኳዋ መልካም ጎሮቤት መሆን እንችላለን ወይ ነው:: እነሱስ ይኸን አሮጌ ሰከንድ ሃንድ ማሽን ገዝተው በትግራይ የተከሉት ፋብሪካ የዛሬውን የዓለም ገበያ የሚመጥን ተፈላጊ ምርት በማምረት እና ኤክስፖርት በማድረግ ብቻ ኑሮውን ይዘልቁታል ወይ ነው ሥጋቴ:: የተዘረፈ ገንዘብ ዘላለም ይበላል ወይ ነው:: ምክንያቱም በማዕከላዊ ገበያ ውስጥ የትግራይ የኢኮኖሚ ድርሻ አይቼ ስለማለውቅ::

ጥራጥሬ: ፍራፍሬ ሥራ ሥር ቡና ከብት ቆዳና ሌጦ ዕብነ-በረድ ውኃ ኤሌክትሪክ /እንደነደፉት ታላቁ የህዳሴ ግድብ በትግራይ ክልል እንዲሆን ካላጸደቁት በስተቀረ/ እውን የወያኔዎች ህልም የጤና ነወይ ነው::

ይኸ የተበደለ: የተገደለ የተገፋ: የተከፋ ሕዝብ እንደጎርፍ ያጥለቀለቃቸው ዕለት ታየኝ:: እነሱ በተራቸው በዋይት ሀውስ ጎዳና ዩ ኤስ ! ሼም ኦን ዩ ብለው የዓለምን ሕዝብ ደጀ ጥናት ሲጀምሩ::ደጅ ጥናት ብቻ ሳይሆኑ እዚያው ደጅ ውለው ያድራሉ እንጂ ንቅንቅ የሚሉም አይመስለኝም::

አንድ ብሄር ላይ ያነጣጠረ እልቂት እየተካሄደብን ነው ብለው ያለማፈር ከበሮአቸውን ይዘው እንደሚጮኹ በዓይነ-ህሊናየ ታየኝ:: ያ- እንዳይሆን የትግራይ ሕዝብ ለወያኔ በስሜ ኢትዮጵያን ሕዝብ አትግደል! በስሜ የኢትዮጵያን እናቶች አታስለቅስ! በስሜ የኢትዮጵያ ጨቅላ ሕጻናትን አትጨፍጭፍ ብለው ለወያኔ ከመናገር ይልቅ በፌስ ቡኮቻቸውና ዌብሳይቶቻቸው ስድባቸውን ያጎርፋሉ:: ልክ የለሽ ንቀታቸውን ያፈስሳሉ:: ትዕቢታቸው ከልክ ማለፉን ያሳያሉ ::

የአፍሪካ አርያን ሕዝብ ለመሆን መጣራቸው በጣም ያሳዝናል:: ይኸ ነው የሚያሰጋኝ:: ዕጣ-ፈንታቸው ነው ያስጨነቀኝ:: ደግ! የሥራቸውን ነው የሚያገኙት ብዬ የእነሱን ጭካኔ ማውረስ አፈልግም:: ይሄን ግፍ የተዋለበትን ተበዳይ ሕዝብ ማነው ተው የሚለው? ማነው እባክህ የሚለው? እነዚህ እኮ የሚሠሩት ሥራ እስከ ሰባት ቤት ዘር ማንዘራቸው የሚዘልቅ የሓጢአት ውርዴ ሰንቀዋል:: ጎበዝ አያሳስብም?? ትግራዊያን ያላዩት ነገ የሚባል ቀን በፍጥነት እየመጣ መሆኑን ነው::

<u>አሁንም ለትግራይ ሕዝብ መልእክትት አለኝ፡፡</u>

ምንም እንኳዋ ጊዜው ቢመሽም ጀምበርዋ ጨርሶ ሳትጠልቅ አስፈሪው ጨለማ ሳይመጣ አሁን ፈጥነው ከ 16 ቱ የትግራይ ተወላጆች እንደቡዳ ባቁላ ከተገኙት ግለሰቦች ምልዓተ- ዙሪያ ተሰባስበው እራሳቸውን ቢያድኑ መልካም ነው::

እሱም ዛሬ!!! አሁን!!!

**ደምለው አልማው**

*http://www.ethiopanorama.com*